

# ጴጥሮስ

ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችባቸው በመጀመሪያዎቹ ዓመታት እግዚአብሔር ለሐዋርያት አስደናቂ ኃይልን ሰጣቸው። የታመሙ ሰዎች ጤናቸውን ያገኙ ነበር። ስለዚህም ብዙ ቤተሰቦች የታመሙ ዘመዶቻቸውን ወደ ሐዋርያት ያመጡና እንዲፈወሱ ያደርጓቸው ነበር።

አንድ ቀን ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ። የምሽት አገልግሎት ጊዜ ነበር። መልካም ተብሎ ወደሚጠራው የቤተ መቅደሱ ደጅም ሄዱ። በዚያም አንድ ለማኝ ነበር። በእድሜው ሁሉ መራመድ የማይችል ሽባ ሰው ነበር። አንዲት እርምጃ እንኳን ተራምዶ አያውቅም።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደእርሱ በቀረቡ ጊዜ ለመናቸው። ስራ መስራት ስለማይችል ለመኖር የግድ መለመን ነበረበት። ጴጥሮስና ዮሐንስ ቆሙና ትኩር ብለው ተመለከቱት። ጴጥሮስም "ወደእኛ እይ።" አሉት። በዚህን ጊዜ ሰውዬው ገንዘብ ይሰጡኛል ብሎ አሰበ። ጴጥሮስም "ብርና ወርቅ የለኝም፤ ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ። በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሰተህ ተራመድ!" አለው።

ይህንን ካለው በኋላም ቀኝ እጁን ይዞ አስነሳው። በዚያችው መቀስበት የሰውዬው ቁርጭምጭሚትና አጥንት ጠነከሩ። ወዲያውኑ ዘለለ። ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋርም ወደ ቤተ መቅደስ እየተራመደ ገባ። እግዚአብሔርንም ስለፈውሱ አመሰገነው።

በዚያ የነበሩ ሰዎችም አዩት። በቤተ መቅደሱ ደጃፍ ተቀምጦ የሚለምነው ሰው መሆኑን ሲያውቁም እጅግ ተደነቁ። እንደማይራመድ ያውቁ ነበር። ይህንን ተዓምር ለማየትም በሰውዬው ዙሪያ ተከማቹ።

ከዚያም ጴጥሮስ ለሕዝቡ ስለኢየሱስ አዳኝነት አስተማራቸው።

ይህ የጴጥሮስና የዮሐንስ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 3፡ 1 – 12 ውስጥ ይገኛል።

http://gardenofpraise.com
Copyright picture courtesy of gospelservices.com